# ፈጣጣ-ለማኝ

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)* *መጋቢት ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም.*

ቃሉ እንደሚያመለክተው ለማኝ በልመና ስራ ላይ የተሰማራ ወይም የሚለምን ሰው ማለት ነው። "ለመነ" ከሚለው ግስ የተራባው ልመና እንደዚሁ የመለመንን ሂደት የሚገልጽ ሲሆን የልመና ሂደትም ዓይነት፣ ዓይነት አለው። አዎ ልመናዎች በባህሪ ቢመሳሰሉም በመልክ ግን ይለያያሉ። የእለት ጉርስን ለማግኘት ወደ ቤተ-ክርስቲያን መሄጃ መንገድ ዳር ወይም ደጀ-ሰላም አጠገብ ቆሞ አለዚያም ቁጭ ብሎ፤ ነጠላን ዘርግቶ በሚያሳዝን ዜማ "ስለጭንቅ አማላጅቱ! ስለወላዲት አምላክ! ስለእመብርሃን! ስለመድሃኒት አለም! ስለፈረሰኛው ጊዎርጊስ! ስለቅዱስ ሚካኤል! ወዘተርፌ " እያሉ መማጸን መለመን ነው። ከመስጊድ መግቢያ በር ላይ ቆሞ "የምቀምሰው የምልሰው የሌለኝ ሞጣጣ ድሃ ነኝና ስለ አላህ ስትሉ ጀባ ብላችሁኝ እለፉ!" እያሉ አንገትን ደፋ አርጎ በትህትና መጠየቅም ልመና ነው። እንደዚሁም በምእራቡ አለም ማርያምን ወይም መድሃኒት አለምን አለዚያም አላህን ሳይጠሩ "ቤት የለሽ" (homless) የሚል ቃል በብጣቂ ካርቶን ላይ ጽፎ መስቀለኛ መንገዶች ላይ መቆምም ልመና ነው። ቤትን ጥርቅም አርጎ ዘግቶ "አምላኬ ሆይ ሽበላዋን ወይዘሪት ወይም ሽበላውን ጎበዝ ዱብ ካደረክልኝ!" ለክብርህ ይህንን ግብር አስገባለሁ" እያሉ ሊከፍሉ የሚችሉትንም ሆነ የማይችሉትን ስለት መሳልም ልመና ነው። በሌላ በኩልም "እንዲያው የእገሌን ወይም የእገሊትን ነገር ሳይውል ሳያድር ካሳየኸኝ ገብስማ ዶሮ አርጄ እጥልልሃለሁ" እያሉ ቆሌን መለማመንም ልመና ነው።

የልመና ባህሪዎች በይዘታቸው ይመሳሰሉ እንጅ የለማኝ አይነቶችና ባህሪዎች ግን አያሌ ናቸው። በእርግጥም አብዛኛው ለማኝ ተፈጥሮ የመስራት አቅምን ነስታው ወይም ብርሃኑን ጋርዳው እንደ ሰው ለመኖር ሲል የሚለምን ነው። ይህ መቼም ሰው ሊበላና ሊጠጣ የሚችለውን ሰርቶ ለማግኘት አቅመ-አልቦ በመሆኑ የሚያከናውነው ጉዳይ ስለሆነ በእኔ እምነት ተገቢ የልመና አይነት ነው ብዬ አስባለሁ። እንዲያውም እናቴ "የተቸገረን የረዳ በምድርም በሰማይ ቤትም የተከበረ ይሆናል" እያለች ሳይታክታት ታስተምረኝ ስለነበር አንደኛ ደረጃ ት/ቤት በነበርኩበት ወቅት ዘወትር ማክሰኞ በምሳ ሰዓት ገበያ ዳር ቁጭ ብለው ፀሐይ እየቆላቸው የሚለምኑ አቅመ-ደካሞችን ውሃ እየቀዳሁ እያጠጣሁ ምርቃት እቀበል ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ሰርቶ መብላት ሳይሳነው በራሱ ስንፍና ወይም ደግሞ ከእርሱ ቁጥጥር ውጭ በሆነ መሰናክል በልመና ስራ ላይ የሚሰማራ ለማኝ አለ። አንዳንዱ እንዲያውም ለዚሁ ብሎ አካሉን ራሱ የሚያጎድል ወይም ፈጣሪ እንዲያጎድልለት የሚመኝ አለ ይባላል። "የልመና ልምድ ያለው ሳይሆን አይቀርም" እያላችሁ አትሙኝ እንጅ በሽተኛ ለመምሰል ሆነ ብለው እግራቸውን ግራሶ የሚቀቡ ለማኞች ገጥመዋችሁ እንደኔ የታዘባችሁ ትኖራላችሁ ብዬ እገምታለሁ። በዚህ መልክ አካሉን አጉድሎ ወይም የበሽተኛ መልክ ሰጥቶ፣ አለዚያም ገላው የጎደለን ሰው ወይም ችጋርና በሽታ የሚያሰቃየውን ሕዝብ ተጠቅሞ በልመና ስራ ላይ የሚሰማራ ሰው ለእኔ ፈጣጣ-ለማኝ ነው።

እንዲያው ወጉ እንዳይቀር እኛ አፍሪካውያን ለማኝና መጽዋች እንባባላለን እንጅ ዛሬ አጢኖ ላስተዋለው የአብዛኛው አፍሪካውያን ሕልውና በአረመኔ አገዛዞች የልመና ባህል ላይ የተመሰረተ ሆኗል። የሚያሳዝነውና የሚገርመው ታዲያ ተፈጥሮ አስተካክሎ የሰራውን አፍሪካን ለማኝ ያደረጉት ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ እንደሚባለው ራሳቸውን "ፕሬዘዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስቴር ወዘተርፌ እያሉ የሚሰይሙ ፈጣጣ-ለማኞች መሆናቸው ነው። እነዚህ ፈጣጣ-ለማኞች (በእውነቱ ነፍስ-ገዳይ ለማኞች ማለትም ይቻላል) ደምን እንደ ጅረት እያወረዱና እሬሳ እየተራመዱ እንደ ቆጥ ከረዘመ ወንበር ላይ ጉብ ይላሉ። ሳይውሉ ሳያድሩም ከሞት የተረፈውን ሕዝብ አይኑን እየጋረዱ- እውር፤ አንደበቱን እየዘጉ- ዲዳ፤ ጆሮውን እየወተፉ-ደንቆሮ፤ ጣቶቹን እያሰሩ- ዱሽ፤ አእምሮውን እያቀወሱ- እብድ ያደርጉታል። እውርነትን ዲዳነትን፣ ድንቁርናንና እብደትን እንደ ማደበሪያ እየመገመጉ እንደ ማይምነት፣ ችጋርና በሽታ ያሉ የሰው ልጅ ጠንቆችም ያገፈግፋሉ (ይፋፋሉ)። ፈጣጣ-ለማኞችም ዘርተው ያመረቱትን ችጋር፣ በሽታና ድንቁርና ይዘው ለልመና ወደ ጀምበር መግቢያ ያንጋጥጣሉ። እንዲያውም አንዳንዴ ፈጣጣ-ለማኞች እያስፈራሩ ገንዘብ አምጡ ይላሉ። "ዶላር፣ፓውንድ ወይም ዩሮ ከመለመኛ ነጠላችን ላይ ዛሬውኑ ዱብ.. ዱብ ካላደረጋችሁ አካባቢው በሽብርተኞች ይጥለቀለቃል"፣ ለህይወት ክብር ያላቸው በመምሰልም "ብዙ ነፍስም ያልቃል" እያሉ በድርቅና ባለገንዘቦችን ያስጠነቅቃሉ። ቀጥቅጠው፣ ፈልጠውና እንደ ተልባ አሽተው ድኩማን ባደረጉት ሕዝብ ስም አፈ-ከርፋፋ ኪሳቸውን ሞልተው፣ በአጸፋው ባለንብረቶቹ የሰጧቸውን የቤት ስራ ለመፈጸም ምለው ይፈርማሉ። ውሻ ፍርፋሪ ያስለመደውን ጌታውን ሲያይ ጅራቱን እንደሚቆላው ሁሉ፤ ፍጥጥ ያሉ ፈጣጣ-ለማኞችም ምእራባውያን መጽዋቾቻቸውን ሲያዩ የሚጥሉላቸውን ልፋጭ ለማየት ይቁነጠነጣሉ። ፍንድቅድቅ ብለውም ፎቶግራፍ አብረው ይነሳሉ።

እንደ ስዊዝ-ባንክ ካሉት የንብረት ማከማቻ ጎተራዎቻቸው ሞልቶ የተረፈውን የልመና ገንዘብ ወደ አገር ቤት ይወስዱና ለሚቀጥለው ልመና ዝግጅት ይጠቀሙበታል። ድሮ አንድ-አይና ያደረጉትን ዜጋ በአካበቱት ልምዳቸው ያለርህራሄ የቀረችውን ብርሃን በሳንጃ ይጠነቁሉና ሙሉ አይነ-ስውር አርገው "እየመራን እንለምንብህ" ይሉታል። ታቻምና አንዱን የጆሮ ታንቡር ያፈነዱበትንም ዘንድሮ ከቻይና በተረጠቡት እራፊ ሌላውን ታንቡሩን ይወትፉና መሰማሚያውን አድልመው እየተቀራረበች ከመጣችዋ አለም አርቀው ያኖሩታል። ቀደም ሲል አንድ እግሩን ሰንክለው አንካሳ ያረጉትን ደግሞ በሌላ እግሩ እግር ብረት ያስገቡና በመቀመጫው እየተንፏቀቀ እንዲኖር ያስገድዱታል። በፊት አንድ እጁን የቆረጡትን ደግሞ

ሌላውንም እጁን በቦንብ ቁምጥ ያደርጉና እንኳን የሚሰራበት ገላውን ሲበላው የሚያክበት ጣትም ይነሱታል። “አካሌን፣ መብቴንና ክብሬን አትንኩ” እያለ አሻፈረኝ ማለት የሚቃጣውን ደግሞ  ከርቸሌ ውስጥ ከተው እንዲሞት አለዚያም በዚህ ጽሑፍ መጨረሻ  በዋቢ አንድ [1] ላይ እንደቀረቡት መከራ ተቀባዮች ሁሉ ጭንቅላቱን ወይም ደረቱን በባሩድ እየፈረከሱ ከምድረ-ገጥ ያጠፉታል።  ወላጅን፣ ልጅን፣ ዘመመድን በጠቅላላው አገርን ደግሞ ጥቁር ለባሽ አድርገው ከዘላለም ሐዘን ውስጥ ይከቱታል። በሞተው፣ በታሰረው፣ በታወረው፣ በደነቆረው፣ መራመድ ባቃተውና በመሪር ሐዘን ውስጥ በተዘፈቀው ገላ ላይ ማይምነት፣ ችጋርና በሽታ እንደ እንጉዳይ መፍላታቸውን ይቀጥላሉ። በእነዚህ የሕብረተሰብ ሰቆቃዎች ላይ የተዋቀረው የማይነጥፍ የልመና ጅረትም ጎልብቶ ወደ ወንዝነት ያድግና ፈጣጣ-ለማኞችን አንሳፎ መልሶ ወደ ምእራቡ አለም ያደርሳቸዋል።። አዙሪት ቀለበቱ (the vicious circle) ይቀጥላል፣ ይቀጥላል.. ይቀጥላል...

በሌላ በኩል ደግሞ ባለንብረቶች አሽከር ወይም ሸርተት ወረድ ብሎ የሚታዘዝ አገልጋይ ስለሚፈልጉ እንደዚሁም ሁሌ ለጋስ መባል፤ ሁሌ መለመን ስለሚወዱ ፈጣጣ- ለማኞችን እንደ በኩር ልጅ ተንከባክበው ይይዟቸዋል። በዚህም ምክንያት የአፍሪካ ሕዝብ ከአለም በፊት ተፈጥሮ ሁሌ ችግረኛ፣ ሁሌ በሽተኛ የሆነበትን ዋነኛ ምክንያት ፈጣጣ-ለማኝ መሆኑን በሚገባ እንደማያወቁ ሁሉ በቀጥታ ሲገዙት የኖሩትን ባርያ በተዘዋዋሪ ለመሸመትና እንደ ፈጣሪ አቤቱ እየተባሉ፤ እየተለመኑ ለመኖር እንዲያመቻቸው ፈጣጣ-ለማኝ እንዳይጠወልግ ውሀ ሲያርከፈክፉበት ይውላሉ። በዚህም መሰረት የህሊና አልማዝ ያልፈጠረባቸውን ወይም በስለት ቢላዋ ከጭንቅላታቸው እንደ ቆዳ ተገፎ የተጣለውና አይናቸውን በቅጥፈት ጨው ሙልጭ አድረገው የታጠቡትን ፈጣጣ-ለማኞች ሳይቀር እነሱ G-20 [2] በሚሉት ስብሰባ ላይ “ቡች ቡች” ብለው ጠርተዋቸዋል። በአለም ላይ በደረሰው የምጣኔ ሐብት ድቀት ምክንያት ተንኮታኩተው እንዳይወድቁ ከወዲሁ በፈጣጣ-ለማኞች ላይ ካፊያ ቢጤ ሊያርከፈክፉባቸው ይመስላል። እንኳንስ ተጠርቶ ሳይነገረውም ድግስን በማነፍነፍ አሽትቶ የሚያገኘው ፈጣጣ-ለማኝም የመለመኛ ከረጢቱን ይዞ ሊበር አኮብኩቧል።

እንዲያው ሲያስቡት ግን ይገርማል። እንደ ልማድ ሆኖ ፈጣጣ-ለማኝ ሕዝብን አታሎም ሆነ በጌቶቹ ተመጽውቶ ምን ኪሱ ቢሞላ፤ ምን ከርሱ ቢወጠር እንደ ቡችላ ከመሬት የወደቀ ፍርፋሪ ለመለቃቀም ጌታውን ሲከተል ይኖራል።


*ዋቢ*

1. *Massacre in Pictures http://www.abbaymedia.com/Remembering_Victims_of_November_2005.htm*
2. *G-20 Summit   http://www.g20.org/*

*Related Readings*

1. *African Union: A misnomer     http://addisvoice.com/article/african_leaders.htm*
2. *Addressing African Rulers     http://addisvoice.com/article/african_rulers.htm*